# የዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰንን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# የዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰንን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ

# ቁጥር 32/2001

የንግድ ስምምነት ለማይመለከታቸው የገቢና ወጪ ዕቃዎች የስሪት አገርን መወሰን ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን ለማስከፈል፣ ለስሪት አገር ምልክቶች እና መለያዎች አጠቃቀም፣ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ፍትሀዊ ያልሆነ ውድድር እንዳይደርስባቸው የኮታ ገደብ ለመጣል ፣ የገቢና ወጪ የንግድ ዕቃዎች ስታትስቲካዊ መረጃ ለመያዝ በማስፈለጉ፣

የንግድ ስምምነት ለሚመለከታቸው የገቢና ወጪ ዕቃዎች የስሪት አገርን መወሰን ኢትዮጵያ ከተፈራረመችባቸው የጋራ ገበያ የንግድ ሥምምነቶች አንፃር የሥሪት አገር ደንቦችን የማያሟሉ ምርቶች የታሪፍ ቅናሽ እንዳይኖራቸው ለማድረግ እና በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተጠቃሚ በምትሆንባቸው የኮታና ቀረጥ ነፃ ልዩ የውጭ ገበያ ዕድል የንግድ ስምምነቶች ተፈፃሚነት በስምምነቶቹ ውስጥ በተቀመጡት የሥሪት ሀገር ደንቦች መሠረት መሆኑን ማሳወቅ ተገቢ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን የሥሪት አገር አወሳሰን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ #የዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰንን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 32/2001; ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል፡-

1) «የጋራ ገበያ» ማለት በምሥራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ ማቋቋሚያ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የጋራ ገበያ ነው፡፡
2) «የምርት ግብዓት» ማለት አንድን ያለቀለት ምርት ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ ዕቃዎች ፣ በከፊል ያለቀላቸው ዕቃዎች፣ ውህዶች እና አካላት ነው፡፡
3) «ልዩ የውጭ ገበያ ዕድል» ማለት በኢኮኖሚያቸው ያደጉት ሀገራት በማደግ ላይ ላሉትና ወደኋላ ለቀሩት ሀገራት የውጭ ንግዳቸውን ለማበረታታት እንዲችሉ የሰጡት የኮታና ቀረጥ ነፃ የውጭ ንግድ ዕድል ነው፡፡
4) «መሠረታዊ ለውጥ(Basic Change)» ማለት በሐርሞናይዝድ ሲስተም የሸቀጦች አመዳደብ ደንብ መሠረት የመጨረሻው ምርት የታሪፍ አንቀፅ ከምርት ግብአቱ የታሪፍ አንቀጽ የተለየ ሲሆን ነው፡፡
5) «አምራች» ማለት ምርቱን የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ጥሬ ዕቃ ተጠቅሞ በማምረት ወይም በጥሬ ዕቃ ደረጃ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነው፡፡
6) "የስሪት አገር" ማለት እቃዎች የተሰሩበትን አገር ለመወሰን የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት ነው፡፡
7) "የስራት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ እቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመሰረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡
8) «ባለሥልጣን» ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
9) «አዋጅ» ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ እና ወደ ውጪ ሀገር በሚላኩ ዕቃዎች ላይ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን

## 4. የንግድ ስምምነት የማይመለከታቸው ዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን መስፈርቶች

1) አንድ ዕቃ በአንድ አገር ተመረተ የሚባለው:-

ሀ. ምርቱ በአምራች አገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተመረተ ሲሆን፣

ለ. ምርቱ በከፊል ከሌላ አገር የገቡ የምርት ግብዓቶችን በመጠቀም የተመረተ እና የምርት ሂደቱ በምርት ግብዓቶቹ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ከሆነ ወይም

ሐ. ከአንድ በላይ በሆኑ አገሮች በተገኘ የምርት ግብአት የተከናወነ ምርት ያለቀለትን ምርት የሥሪት አገር ለመወሰን ሲባል፣ የመጨረሻ የምርት ሂደት የተከናወነበት አገር በምርት ግብአት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ከሆነ ነው፡፡

2) በአንድ አገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተመረቱ ወይም የተገኙ ተደርገው የሚቆጠሩ ምርቶች፣

ሀ/ ከአንድ አገር መሬት ወይም የባህር ወለል ተቆፍረው የወጡ ማዕድናት፣

ለ/ በአንድ አገር ውስጥ የተመረቱ የእርሻ ምርቶች፣

ሐ/ በአንድ አገር ውስጥ የተወለዱና ያደጉ እንስሳትና ተዋፅኦዎቻቸው፣

መ/ ከአደንና ከአሳ ማስገር ሥራ የተገኙ የምርት ውጤቶች፣

ሠ/ ከአንድ አገር የባህር ክልል፣ ከሐይቅ፣ ከወንዝና ከሌላ የውሃ አካላት የአገሩን መርከብ በመጠቀም የተገኙ የምርት ውጤቶች፣

ረ/ ከላይ በፊደል ተራ "ሠ" የተጠቀሱትን የምርት ውጤቶች ብቻ እንደ ግብዓት በመጠቀም የተመረቱ ምርቶች፣

ሰ/ በአንድ አገር ውስጥ አገልግሎት ላይ ውለው የነበሩ አሮጌ ውዳቂ ዕቃዎች፣

ሸ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል ተራ "ሀ" እስከ "ሰ" የተጠቀሱትን በመጠቀም በአንድ አገር የተመረተ ምርት፣

3) በምርት ሂደት ውስጥ ሥራ ላይ የዋሉ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ነዳጅ፣ የማምረቻ ህንፃ፣ ማሺነሪ እና የእጅ መሣሪያዎች ላለቀለት ምርት የሥሪት አገር አወሳሰን በዛው አገር ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተመረቱ ወይም የተገኙ ተደርገው ይወሰዳሉ፣

## 5. በንግድ ስምምነት የሚካተቱ ዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን

1) የጋራ ገበያ የገቢና ወጪ ዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን በንግድ ስምምነቱ የሥሪት አገር አወሳሰን መስፈርት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2) በአለም አቀፍ ስምምነት ኢትዮጵያ ተጠቃሚ የምትሆንበት ልዩ የውጭ ገበያ የኮታና ቀረጥ ነፃ ወጪ ዕቃዎች የሥሪት ሀገር አወሳሰን በስምምነቱ የሥሪት ሀገር አወሳሰን መስፈርት መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 6. የምርት ግብዓት ይዘት እና ዋጋ

1) ማንኛውም የምርት ግብዓት ሙሉ በሙሉ በአንድ አገር የተመረተ ወይም ከአንድ አገር የተገኘ ከሆነ፣ ከሌላ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ በውስጡ ያላካተተ ተደርጐ ይወሰዳል፣
2) ከውጪ አገር የገባ የምርት ግብዓት ዋጋ በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኘ የዕቃው የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ነው፣
3) ከውጪ አገር የገባውን የምርት ግብዓት በጉምሩክ ተቀባይነት ያገኘ የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ማግኘት ካልተቻለ፣ ወቅታዊ የሆነ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ የምርት ግብዓቶችን የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ መውሰድ ይቻላል፣
4) በምርት ተግባር ላይ የዋለን የምርት ግብዓት የሥሪት አገር ማረጋገጥ ካልተቻለ በሌላ አገር እንደተመረተ ተደርጐ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ያላቸው አገሮች ዋጋ ይወሰዳል፡፡

## 7. የሥሪት አገር ደንብን የማያሟሉ የምርት ሂደቶች

የሚከተሉት የአሰራር ሂደቶች የታሪፍ አመዳደብ ለውጥ የሚያስከትሉ ሆኑም አልሆኑም ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን የስሪት አገር ለመወሰን ከግምት አይገቡም፡፡

1) ማሸግ፣ በጠርሙስ መሙላት፣ በፍላስኮች፣ በከረጢቶች፣ በሣጥኖች ውስጥ መክተት እና መሰል የእሽጋ ሥራዎች፣

2) ከሌላ አገር የመጡ ውህዶችን ማደባለቅ፣
3) ከሌላ አገር የመጡ ውህዶችንና አካላትን በመጠቀም የሚከናወኑ የመቀላቀል እና የመገጣጠም ሥራዎች፣
4) በምርት ማጓጓዝ እና ክምችት ወቅት ምርቱን ባለበት ሁኔታ ለማቆየት የሚከናወኑ የማናፈስ፣ የማስጣት፣ የማድረቅ፣ የማቀዝቀዝ፣ የማጠን፣ እና በኬሚካል የመንከርና የመዘፍዘፍ ሥራዎች፣
5) ማሸጊያዎችን የመለወጥ እና ዕቃዎችን መልሶ የማሸግ ሥራዎች፣
6) በዕቃዎችና በማሸጊያዎቻቸው ላይ ምልክቶችንና መለያዎችን ማድረግና ማተም፣
7) ቀላል የሆኑ አቧራ የማራገፍ፣ የማበጠር፣ የመለየት፣ የማጠብ፣ ቀለም የመቀባትና የመቆራረጥ ሥራዎች፣
8) የእንስሳት እርድ፣

## 8. የዕቃው አካል ተደርገው የሚወሰዱ፣

ከዚህ በታች የተመለከቱት የዕቃው አካላት ተብለው ይወሰዳሉ፡፡

1) በአንድ ጭነት ውስጥ የተጠቃለሉ የተለያዩ ዕቃዎች የሥሪት አገርን ከማረጋገጥ አንፃር ለየብቻቸው ይታያሉ፣
2) በሐርሞናይዝድ ሲስተም የሸቀጦች አመዳደብ መሠረት በአንድ ላይ ተጠቃለው የሚታዩ ዕቃዎች ከሆኑ፣
3) ዋጋቸው ከዕቃው ዋጋ ጋር ተጠቃሎ የቀረበ የእጅ መሣሪያዎችና ተጓዳኞች፣
4) ከትራንስፖርት እና ከምርት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ተለያይተው በተለያዩ ጭነቶች ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች፣

## 9. በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ግብዓቶችን መለያየት

የዕቃዎችን የሥሪት አገር ለመወሰን ሲባል አምራቹ አንድ ዓይነት ባህሪ፣ ነገር ግን የተለያየ የሥሪት አገር ያላቸውን ግብዓቶች በአካል ለመለያየት ካልቻለ፣ አካላዊ መለየቱ በዓለም አቀፋዊ የስሪት አገር ማረጋገጫ ስርዓት ተቀባይነት ባለው የሂሣብ ስሌት ላይ በተመሠረተ ዘዴ ሊተካ ይችላል፣

## 10. ማሽጊያዎች

1) ለጉምሩክ ቀረጥ ሲባል ዕቃውና ማሸጊያው ተለያይተው የሚታዩ ከሆነ፣ የማሸጊያ ማቴሪያሉ የሥሪት አገር ተለይቶ ሊወሰን ይችላል፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠው ተግባራዊ በማይሆንበት ጊዜ የማሸጊያ ማቴሪያሉ የዕቃው አካል ተደርጐ ይወሰዳል፣ የዕቃው የሥሪት አገር ሲወሰንም በዚሁ ላይ በመመሥረት ይሆናል፣
3) ዕቃዎችን ለማጓጓዝ እና በጊዜያዊነት ለማከማቸት የሚያገለግሉ ተመላሽ ኮንቴይነሮች ተመልሰው ከአገር ካልወጡ ለሥሪት አገር አወሳሰን በውስጣቸው ከታሸጉት ዕቃዎች ተለይተው ይታያሉ፣

# ክፍል ሶስት

# ስለዕቃዎች የሥሪት ሀገር ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

## 11. የሥሪት አገር የሠነድ ማረጋገጫ

1) ዕቃዎች የሥሪት አገር ደንቦችን አሟልተው በአንድ አገር ውስጥ መመረታቸውን ለማረጋገጥ፣ በላኪው ተሞልቶ ወይም በላኪው አገር ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠ፣ የተፈረመ እና ማህተም የተደረገበት የሥሪት አገር ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፣
2) ባለሥልጣኑ ወደ አገር የገባው ዕቃ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት የቀረበለት ቢሆንም፣ በዕቃው የሥሪት አገር ላይ ጥርጣሬ ካለው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሠረት አስፈላጊውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል፣
3) ባለሥልጣኑ በዕቃው የሥሪት አገር ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው አስፈላጊውን ዋስትና በመያዝ እንደ አግባብነቱ ናሙና በማስቀረት ዕቃውን መልቀቅ ይችላል፣
4) በሠርቲፊኬቱ ላይ የሚታዩ ጥቃቅን የጽህፈት ግድፈቶች በአስመጪው አስፈላጊው ማስተካከያ እንደተደረገባቸው የሚገልጽ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ ሠርቲፊኬቱን ዋጋ ላያሳጣው ይችላል።

## 12. የሥሪት አገር ሠርቲፊኬቶችን ለማግኘት የሚከናወኑ ተግባሮች፣

ወደ ውጪ ለሚላክ ዕቃ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ለማግኘት ላኪው የሚከተሉትን መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1) ባቀረበው ማመልከቻ መሠረት የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት የተጠየቀባቸው ምርቶች የስሪት ሀገር መስፈርቶቻቸውን ያሟሉና ተቀባይነት ያገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
2) በተሰጠው ማረጋገጫ መሠረት ለእያንዳንዱ ጭነት ራሱን የቻለ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት መሙላት
3) ሠርቲፊኬቱን ከኤክስፖርት ዲክላሬሽንና ከሌሎች ደጋፊ ሰነዶች ጋር አያይዞ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ማቅረብ፣

## 13. ሥልጣን የተሰጠው የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠጪ አካል ተግባር፣

1) የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬቱ በበቂ ኮፒ ተሞልቶ መቅረቡን ማረጋገጥ፣
2) ሠርቲፊኬቱ ሙሉ በሙሉ እና በትክክል ተሞልቶ መቅረቡን ማረጋገጥ፣
3) በሠርቲፊኬቱ ላይ የተዘረዘሩት ምርቶች የሥሪት አገር ደንብን የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
4) በሠርቲፊኬቱ ላይ የተሞሉትን ፍሬ ነገሮችና አሐዞች በኢንቮይሱ ላይ ከሠፈሩት ጋር በማነፃፀር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
5) ሠርቲፊኬቱ በትክክል የተሞላ መሆኑ ሲረጋገጥ ፊርማና ማህተም ማድረግ፣

## 14. የሥሪት አገር ሠርቲፊኬቶችን ትክክለኛነት ማጣራት፣

ባለሥልጣኑ፡-

1) የገቢ ወይም የወጪ ዕቃን የሥሪት አገር በተመለከተ አስመጪው/ላኪውን ባቀረበው ማስረጃዎች ላይ ጥርጣሬ ካለው፣ ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይችላል፤
2) ተጨማሪ ደጋፊ ማስረጃዎች ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የመረጃ መቀበያ ቅጽ ላይ በትክክል ተሞልተው መቅረባቸውን ያጣራል፤
3) ከላኪው አገር የተላኩት ተጨማሪ መረጃዎች አጥጋቢ ሆነው ካላገኛቸው በላኪው አገር በመገኘት አስፈላጊውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል፤
4) በላኪው አገር በመገኘት የሚያደርገውን ማጣራት በተመለከተ በላኪው አገር ሥልጣን ከተሰጠው አካል ጋር ሊመካከር ይችላል፤

5) ፊርሞ የሚያወጣቸውን የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬቶች የዕቃዎቹ የሥሪት አገር ደንቦችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ አምራቹ ወይም ላኪው ተጨማሪ ማስረጃዎችን እንዲያቀርብ ወይም በሥራ ቦታ በመገኘት አስፈላጊውን ማጣራት ማድረግ ይችላል፤

6) ከተቀባይ አገር ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብ ወይም ማጣራት እንዲደረግ ጥያቄ ሲቀርብ ከተቀባዩ አገር የሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በአምራቹ ወይም በላኪው የሥራ ቦታ በመገኘት ማጣራት ያደርጋል፣ ወይም የተጠየቀው መረጃ እንዲላክ ያደርጋል፣

7) አምራቹ ወይም ላኪው የተጠየቀውን መረጃ በወቅቱ ማቅረቡን፣ በሥራዉ ቦታ በመገኘት ለሚደረግ ማጣራት አስፈላጊውን ትብብር ማድረጉን ያረጋግጣል፣

## 15. ለጠረፍ ንግድ የሚያገለግል ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት

የጠረፍ ንግድን ለማሳደግ ከጎረቤት አገሮች ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት እንዲቀርብ የተወሰነ እንደሆነ በሚከተለው ሁኔታ ተፈፃሚ ይደረጋል፡-

1) ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬቱ ቅርበት ባለው የጉምሩክ ጣቢያው ተፈርሞ እንዲወጣ ይደረጋል፣

2) በጠረፍ ንግድ ውስጥ ተፈላጊ የሆኑ በየአገሮቹ ሙሉ በሙሉ የተመረቱ ወይም የሥሪት አገር ደንብን የሚያሟሉ ተጨማሪ የምርት ሂደት የተከናወነባቸው ዕቃዎች ዝርዝር ከጎረቤት አገሮች ጋር በጋራ ይዘጋጃል፣

3) በጠረፍ ንግድ የተሠማራ ማናቸውም ሰው ለጠረፍ ንግድ የተዘጋጀውን ልዩ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት በመሙላት ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በቅርብ ለሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ ማቅረብ አለበት፣

4) በቅርብ የሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ ዕቃዎቹ በጠረፍ ንግድ የዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን እና የሥሪት አገር መስፈረቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ በሠርቲፊኬቱ ላይ ፊርማ እና ማህተም ማድረግ አለበት፣

5) ከጎረቤት አገሮች ጋር በጠረፍ ንግድ ላይ በተደረሰበት ስምምነት መሠረት ዕቃዎች ከጎረቤት አገር ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ፣ በቅርብ የሚገኘው የጉምሩክ ጣቢያ በጠረፍ ንግድ የሥሪት አገር ማረጋገጫ ሠርቲፊኬቱ ላይ

የተዘረዘሩት ዕቃዎች በጠረፍ ንግድ የዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

6) በሠርቲፊኬቱ ላይ የተፈረመው ፊርማ እና ማህተም የላኪው አገር ሥልጣን የተሰጠው አካል ከላኪው የፊርማ እና የማህተም ናሙና ጋር አንድ አይነት መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 16. <u>መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን</u>

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ____________ ቀን 2001 ዓ.ም

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር